

## 30-2

# ከእውነት ለሚሸሽ፥ እግዚአብሔር መልስ አለው

### ስውር ሽሽት

በአገልግሎት ውስጥ እያለን የምንሸሸው ሽሽት አለ። ጌታ ወደ አገልግሎት ሲጠራን ጥሪውን ተቀብለን በንጹህ ሕሊናና በንጹህ መንፈስ አገልግሎታችንን እንጀምራለን። በአገልግሎት ውስጥ በቆየን ቁጥር ግን ቀስ በቀስ መስመር እየለቀቅን እንሄዳለን። በብዙ አቅጣጫ በስጋችን ድሎት ይሰማናል። “ይህን ሡራህ፣ ያን አልሡራህም” እያለ የሚጫነን አለቃ ስለሌለብን በመጠኑም ቢሆን መዝናናት እንጀምራለን። ሌሎች ነገሮች ጊዜያችንን ስለሚሻሙን ለምንሰብከው ስብከት ለምናስተምረው ትምህርት የምንዘጋጅበት በቂ ጊዜ ስለሌለን ድሮ የሰበክናቸውን ስብከቶች መላልሰን መስበክና ማስተማር እንጀምራለን። በፊቱ ቀርበን እግዚአብሔር ለሕዝቡ በወቅቱ ምን ለመናገር እንደሚፈልግ በመጠየቅ ፈንታ፣ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው አስመስለን የራሳችንን ሃሳብ ለሕዝቡ ማስተላለፍ እንጀምራለን። ሕዝቡ ይህን ያህል ለይቶ ባያውቀውም እኛ ግን የድብ ብቆሽ ጨዋታ መጫወታችንን ሕሊናችን ካልደነዘዘብን በቅር በደንብ እናውቃለን። ሕዝቡ ቢያውቅም “ምን ቸረገኝ’ ስለሚልና ቅር መሰኘቱን ስለማይገልጽ፣ በወቅቱ መንቃት አንችልም። በዚህ መንፈስ ከቀጠልን በአገል ግሎት ውስጥ ያለን ይምሰለን እንጂ ከአገልግሎት እየሸሸን መሆናችንን አንዘንጋ።

በሌላ አቅጣጫ ደግሞ ከሰዎች ዘንድ በምናገኘው ሙገሳና ክብር ልባችን እንዲሞላ ከፈቀድንለት ቀስ በቀስ የአገልግሎታችን ዓላማ መልኩንና ጠበዩን እየለወጠ ይሄዳል። ጥረታችን የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲ ስፋፋ በመሆን ፈንታ የራሳችንን ስምና ዝና ማስፋፋት ይሆናል። በአገልግሎት ውስጥ እንኑር እንጂ ከአገል ግሎት ውጪ መሆናችንን ሕሊናችን ይመሰክርልናል። በአጠቃላይ፥

- የምናገለግለው ከልባችን አይደለም፤ የነፍሳት ፍቅር የለንም፤ ትኩርታችን በአካባቢያችን በምናገኘው ሥልጣንና ክብር ላይ ነው።
- የነዋይ ፍቅር የስልጣን ትግል ጉልበታችንን ወስዶታል።
- ቅድስና በሌለው ሕይወት ውስጥ ስለምንኖር የአገልግሎት መልክ አለን እንጂ ኃይል የለንም። አገልግሎ ታችንን እንደ ሥራ (ፕሮፌሽን) አድርገን ወስደነዋል።

### ግልጽ የሆነ ሽሽት

2ኛው ደግሞ ስውር ያልሆነ ግልጽ ሽሽት ነው። ብዙዎች ከአገልግሎት ለመሸሽ የሚሞክሩበት የራሳቸው የሆነ ምክንያት አላቸው። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ፥

- በኑሮዬ ጎስቋላ አደረገኝ ሌላ ሥራ እየሠራሁ በትርፍ ጊዜዬ ባገለግል ይሻለኛል።
- የማገለግላቸው ነፍሳት ብዙዎች አይደሉም፣
- ብዙ ትግልና ውጊያ ከክርስቲያኖች ደረሰብኝ፣
- የአገልግሎቴን ውጤት ማየት አልቻልኩም፣
- ከእኔ የተሻሉ ሌሎች ሰዎች ይሥሩት በማለት ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎታቸው የሚሸሹ አሉ።

### ዳዊት ከእውነት ለመሸሽ ያደርገው ሙከራ

እግዚአብሔር ከዝቅተኛ ሥፍራ አንስቶ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ካደራሳቸው ሰዎች መካከል አንደኛው ዳዊት ነበር። ከበግ ጠባቂነት አንስቶ የእሥራኤል ሕዝብ መሪ አደረገው። ዳዊት ከእግዚአብሔር የተደረገለት ውለታ እጅግ ከፍ ያለ ነበር። በሚያሳድዱት ጠላቶቹ ሁሉ ላይ ድልን ሰጠው። ዳዊት በመሠረቱ ብዙ ስለተደረገለት

ብዙ ይጠበቅበታል። እርግጥ ነው ዳዊት ቅን የሆነ ልብ ስለነበረው እግዚአብሔርም ቅንነቱን አውቆ "እንደ ልቤ የሚሆንልኝ ዳዊትን አገኘሁ" ሲል መስክሮለታል። ይሁን እንጂ ዳዊት አንድ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በደከመበት ወቅት ይሆናል ከእውነት ለመሸሽ እንደሞከረ እናያለን። እግዚአብሔር ለዳዊት ብዙ ነገር አትረፍርፎ ሰጥቶት ነበር። በአንድ ጊዜ በዙሪያው ውብ የሆኑ ሺ ሴቶች ማሰለፍ ይችል ነበር። ይሁን እንጂ ዳዊት የራሱ የሆኑትን ማየት ትቶ የራሱ ያልሆነውን መመልከት ሲጀምር፥ እራሱን ማውጣት ከማይችልበት ወጥመድ ውስጥ ገባ። ዳዊት በወቅቱ ለቀረበለት ፈተና ሳይታገል በቀላሉ እጁን እንዳልሰጠ እንገምታለን። ይሁን እንጂ በመጨረሻ ተሸንፎ በጦር ሜዳ በታማኝነት በመታገል ላይ የነበረውን የኦርዮንን ሚስት አስመጥቶ አመነዘረ።

ዳዊት እውነትን ለመሸፈን ያደረገው ሙከራ በግልጽ መታየት የጀመረው ከዚህ በኋላ ነው። ከእሥራኤል ሕዝብና ከእግዚአብሔር ኃጢአቱን ለመሸፈን ሞከረ። ይሁን እንጂ እንዳሰበው አልሆነለትም። ኃጢአቱን ለመደበቅ ያደርገው የመጀመሪያ ሙከራው መስመር እንዳልያዘለት ሲረዳ ሌላ ከባድ እርምጃ ወሰደ። ያም ኦርዮንን በማስገደል ለመጨረሻ ጊዜ ኃጢአቱን ቆፍሮ ለመቅበር ያደርገው ሙከረ ነው። ለጊዜው ፕላኑ የሠራለት መስሎ ተሰማው። ኦርዮን እንደ ሞተ የኦርዮንን ሚስት ለራሱ ወስዶ ሚስቱ አደረጋት። ይሁን እንጂ እውነት በሀሰት ሲሸፈን የማይወደው እግዚአብሔር የዳዊትን ኃጢአት በነብዩ ናታን አማካኝነት እንዲገለጥና በእሥራኤል ሕዝብ ሁሉ ዘንድ እንዲታወቅ አደረገ። በዘመናችን በዚህ ዓይነት እውነትን ለመደበቅ የሚሞክሩ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። ነብዩ ናታንን የመሳሰሉ ነብያት በዘመናችን በመታጣታቸው ይሆን የብዙዎች የተደበቀ ሕይወት የማይጋለጠው? እውነቱ ለጊዜው የተደበቀ ይምሰል እንጂ የእግዚአብሔር ትዕግሥት ሲያበቃ አንድ ቀን በይፋ መገለጡ አይቀርም። እግዚአብሔር ለምን ያህል ጊዜ በትዕግሥት ዝም እንደሚል አናውቅም። ተመሳሳይ የድብብቆሽ ሕይወት ይኖሩ ከነበሩት መካከል እነ ጂም ቤከር ከስምንት ዓመት ትዕግሥት በኋላ ከተደበቁበት ወጥተው ከነኃጢአታቸው በዓለም ሕዝብ ሁሉ ፊት እንዲታወቁ አደረገ። ስማቸውን የጠቀስነው በእነዚህ ሰዎች ለመፍረድ ሳይሆን ታሪካቸው ለብዙዎቻችን አዲስ ባለመሆኑ ብቻ ነው።

## እውነትን ሸፍነን አንኖርም ያሉ

### 1) ዮሴፍ

ዮሴፍ ልክ እንደ ዳዊት ከእግዚአብሔር እጅ ብዙ በረከት የተቀበለ ሰው ነበር። በተለያየ ችግር ውስጥ ሲያልፍ የእግዚአብሔር ጥበቃና እርዳታ አልተለየውም። ወንድሞቹ ከጣሉት ጉድጓድ ውስጥ አውጥቶ በጶጢፈር ቤት ዋና አድርጎ አቆመው። በሰው ሁሉ ፊት ሞገስን ሰጠው። ሰይጣን ግን እግዚአብሔር የሰጠውን መወደድ ያንኑ ወስዶ በመጠቀም የራሱን ዓላማ መፈጸሚያ ሊያደርገው ሞከረ። እግዚአብሔር መወደድን ስለ ሰጠው የጶጢፋር ሚስት ዮሴፍን ወደደቸው። ይሁን እንጂ ዮሴፍን የወደደችበት መንፈስ የተበላሸ በመሆኑ ያ መንፈስ ለዮሴፍ መወደድን ከሰጠው አምላኩ ጋር እንዲያጣላው እራሱን ለዚያ መንፈስ አሳልፎ አልሰጠም። ዮሴፍ መልከ መልካምነትንና መወደድን ያገኘው በራሱ ኃይል ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተቀበለው ነው። ይህንኑ ስጦታ በመጠቀም ሰይጣን ሊያጠፋው ሲሞክር እናያለን። ሰይጣን አማኞችን የሚዋጋው ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚሰጣቸውን ታላላቅ ስጦታዎች በመጠቀም ነው።

ዮሴፍ እውነትን ሸፍኖ ለመኖር በጣም አመቺ ቦታ ላይ ነበር። ከቤተሰቡ ውጪ ስለሚኖር "ዘመዶቼ ያዩኛል" የሚል ፍርሃት አለነበረበትም። "ጶጢፋር ይይዘኛልም" እንዳይል ጶጢፋር በሥፍራው አልነበረም። ሁኔታውን የቀሰቀሰችው የጶጢፋር ሚስት እራሷ በመሆኗ ድርጊታቸው እቤት ውስጥ በነበሩት ሠራተኞች ዘንድ እንዳይታወቅ ዘዴ መፍጠር ስለምትችል የዚያ ፍርሃት እንደማይኖርበት ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ዮሴፍን በእውነት ላይ አምጾ እንዳይኖር የገታው ሁለት ነገር ነው። አንደኛው፥ በጎ ላደረገለት ጶጢፋር ታማኝ ለመሆን ስለፈለገ ነው። "ጌታዬ ሁሉንም ነገር በእኔ ኃላፊነት ሥር ስላደርገ በቤቱ ውስጥ ስላለው ንብረት ሁሉ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም ያለውን ንብረት ሁሉ እንዳስተዳድርለት በአደራ ለእኔ ሰጥቶኛል። ጌታዬ በዚህ ቤት ባለው ንብረት ሁሉ ላይ ከእኔ የበለጠ ኃላፊነት የለውም ከአንቺ በቀር በእኔ ቁጥጥር ሥር ያላደረገው ምንም ነገር የለም ይሄውም ሚስቱ ስለ ሆንሽ ነው" አላት (ዘፍ. 39፥8-9)። ዮሴፍ በጎ ያደርግለትን ሰው ሚስት ተደብቆ መንጠቅ ትክክል አለመሆኑን ስለአመነበት "እምቢ" አለ። ሁለተኛ፥ የእግዚአብሔር ውለታ ነው። "ይህን አስከፊ ኃጢአት በመፈጸም እግዚአብሔርን እንዴት አሳዝናለሁ" አለ። ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የቅርብ ግንኙነት ያፈርስብናል። ብዙ የዋለልንን ጌታ ማሳዘን ስለሚሆን ምንም ያህል እውነትን ለመሸፈን የምናደርገው ሙከራ ባይታወቅብንም እርሳችንን ከተደበቀ ኃጢአት ነጻ ለማድረግ እንሞክር።

## 2) ዳንኤል

ከአምላካቸው ጋር ቅርብ ግንኙነት ከነበራቸው ሰዎች መካከል አንዱ ዳንኤል ነበር። ዳንኤል ጣኦት በሚያመልኩ አሕዛብ መካከል ይኖር ነበር። እነርሱ ለሚያመልኩት አምላክ መጎንበስ በሕዝብ ፊትም ሆነ ለብቻው የሚሆንለት ነገር አይደለም። የከሰሱት ጣላቶቹ በእምነቱ በኩል ካልመጡበት በስተቀር በሌላ አቅጣጫ እንከን ሊያገኙበትና ሊከሱት እንደማይችሉ ያውቁ ነበር። ለዚህ ነው ትክክል የማይመስል ሕግና ደንብ ንጉሡ እንዲያወጣ የገፋፉት። "ለ30 ቀን ያህል ማንም ከንጉሡ በስተቀር ለሌላ አምላክ እንዳይሰግድ" የሚል አዋጅ አሳወጁ። ዳንኤል ይህ አዋጅ የወጣው እርሱን ወጥመድ ውስጥ ለመክተት እንደሆነ ለመረዳት አላስቸገረውም።

ዳንኤል አዋጁን የተቀበለ መስሎ ተደብቆ መጸለይ ይችል ነበር። ወይንም የተባለው ጊዜ እስኪያፍ ድረስ ሕይወቱን ከሞት ለማድዳን ሲል ብቻ መጸለዩን ሊያቋርጥ ይችል ነበር። ዳንኤል ግን እውነትን ለመሸሽግ የማይወድ ትክክለኛና ቀጥተኛ ሰው ነበር። ከአምላኩ ጋር የነበረውን የቅረበ ግንኙነት እንዳያደርግ ወሳኙ ሰው እንዳልሆነ በፍጹም ልቡ ያምናል። ለብቻው ሲሆን የሚያደርገውን በሕዝብ ፊት ለማድረግ ወደ ኋላ የሚል ሰው አልነበረም።ይህም ዳንኤል ሁለት ዓይነት መልክ የነበረው ሰው እንዳልነበረ ያሳያል። በአጠቃላይ ዳንኤል ከእግዚአብሔርና ከከሰሱት ሰዎች እውነት ለመሸፈን ስላልፈለገ እንደተለመደው መስኮቱን ከፍቶ በቀን ሶስት ጊዜ መጸለዩን ቀጠለ። ስለ ሕይወቱ ድህንነት ጥበቃ ኃላፊነቱ የእግዚአብሔር እንጂ የእርሱ እንዳልሆነ ያውቃል። ከእርሱ የሚፈለግበት ከአምላኩ ጋር ግብዝነት በሌለበት መንፈስ የተቀራረበ ግንኙነት መፍጠር ነው። ዳንኤል በእርሱ በኩል የሚፈለግበትን ድርሻ ሲያሟል እግዚአብሔር ደግሞ የማዳኑን ኃላፊነት አከናወነ። ጠላቶቹ እንዳሰቡት በአንበሳዎች ተቦጫጭቆ አልቀረም። አምላኩ የአንበሳዎችን አፍ ዘጋ። እነርሱ ግን ለዳንኤል በማሱት ጉድጓድ ወድቀው የሕይወታቸው ማብቂያ ሆነ።

.........................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እንክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**